# ለእግዚአብሔር ፍቅር

“ … እኔ የሚረባህን ነገር የማስተምርህ በምትሄድባትም መንገድ የምመራህ አምላክህ እግዚአብሔር ነኝ።” (ኢሳ 48 ÷ 17)
God's Love, P.O.Box 6734, Lee’s Summit MO 64064, USA. / E-mail – hello@ethiogodslove.org

ጥር 1996 January 2004 “ልጆችሽም ሁሉ ከእግዚአብሔር የተማሩ ይሆናሉ፡ የልጆችሽም ሰላም ብዙ ይሆናል።” (ኢሳ 54÷13)
አዘጋጅ ፦ መላኩ ማሞ ትዕዛዙ

## “ተነሣና ተመላለስ”

“ጴጥሮስና ዮሐንስም በጸሎት ጊዜ በዘጠኝ ሰዓት ወደ መቅደስ ይወጡ ነበር።ወደ መቅደስም ከሚገቡት ምፅዋት ይለምን ዘንድ ሰዎች ተሸክመው መልካም በሚሏት በመቅደስ ደጅ በየቀኑ ያስቀምጡት የነበሩ *ከእናቱ ማኅፀን ጀምሮ አንካሳ የሆነ አንድ ሰው ነበረ* እርሱም ጴጥሮስና ዮሐንስ ወደ መቅደስ ሊገቡ እንዳላቸው ባየ ጊዜ÷ምጽዋትን ለመናቸው። ጴጥሮስም ከዮሐንስ ጋር ትኩር ብሎ ወደ እርሱ ተመልክቶ፦ ወደ እኛ ተመልከት አለው። እርሱም አንድ ነገር ከእነርሱ እንዲቀበል ሲጠብቅ ወደ እነርሱ ተመለከተ። ጴጥሮስ ግን፦ ብርና ወርቅ የለኝም፤ ይህን ያለኝን ግን እሰጥሃለሁ በናዝሬቱ በኢየሲስ ክርስቶስ ስም ተነሣና ተመላለስ አለው። በቀኝ እጁም ይዞ አስነሣው፡ በዚያን ጊዜም እግሩና ቍርጭምጭምቱ ጸና÷ ወደ ላይ ዘሎም ቆመ፤ይመላለስም ጀመር ፤ እየተመላለሰም እየዘለለም እግዚአብሔርን እያመሰገነ ከእነርሱ ጋር ወደ መቅደስ ገባ።” (የሐዋሪያት ሥራ 3÷1–8)



ስለ ማንነትህ ቆም ብለህ አስበህ ታውቃለህ? ምን ዓይነት ሰው ነህ? ከላይ እንዳነበብነው እንደ አንካሳው ሰው ያሉ፡ ከአንካሳነታቸውና ከጉድለታቸው (ከችግራቸው) የተነሣ÷ ልባቸው ተሰብሮ ተስፋ በመቁረጥ የሚኖሩ ሰዎች ጥቂት አይደሉም። በሽታቸው እንደ ማይፈወስ÷ መከራቸውም እንደማያልፍ ተቀብለው ፡ በሽንፈት ይኖራሉ። ስለዚህም የፈውስ ጉብኝት ከጌታ ሲመጣላቸው ፈጥኖ ለመቀበል የዕምነት አቅም አይኖራቸውም።

ከመጽሐፍ ቅዱስ የጠቀስነው፦ በመቅደስ ደጅ የሚለምነው አንካሳ ሰው፡አንካሳ የሆነው በአደጋ ወይም በበሽታ አይደለም። ከቤት ጣሪያ ወይም ከፈረስ ላይ ወድቆ ተሰብሮም አልነበረም። “ከእናቱ ማኅፀን ጀምሮ አንካሳ የሆነ ነበረ”። ዕድሜውን በሙሉ ከስንኩልነት በቀር ስለ ራሱ ሌላ አያውቅም። የእግሮቹና የቍርጭምጭምቱ አጥንቶች ከተወለደ ጀምረው ጠንክረውለት አያውቁም። ይሁን እንጂ ይህ ሰው ከብዙዎች የተሻለበት ነገር ነበረው፡ ችግሩን ያውቃል። ሸባነቱ ለሌሎች ብቻ ሳይሆን ለእርሱ ለራሱም ግልጽ ነበረ። መደበቅ የሚቻል ዓይነት ቸግር ስላልሆነ በየዕለቱ ተጋፍጦት ይኖር ነበር።

ይሁን እንጂ መንፈስ ቅዱስ በጴጥሮስ በኩል፦ በናዝሬቱ በኢየሱስ ክርስቶስ ስም ተነሣና ተመላለስ ባለው ጊዜ÷ይህ እንዴት ሊሆን ይችላል ሳይል÷በዕምነት ተቀብሎ ለመነሣትና ለመመላለስ ችሎአል።

ዳሩ ግን ብዙ ሰዎች ሸባነታቸውን ወይም ጉድለታቸውን አያስተውሉም። ካስተዋሉም የማይፈወስ መስሎአቸው ይክዳሉ ወይም ሰው አውቆባቸው እንዳይገምታቸው ይደብቃሉ እንጂ መፍትሔ አይሹም። አንዳንዶች ደግሞ ራሳቸውን ሲመለከቱ ምንም ጉልሕ ጉድለት ስለማይታያቸው ወይም ከወገኖች መሐከል ደፍሮ የሚወቅሳቸው ወዳጅ ስለማይገኝ “ደኅና ነኝ”ብለው ያስባሉ። እንደ ዕውነቱ ከሆነ ግን ማንኛውም ሰው በአንድም ሆነ በሌላ፦ ሸባነት (ጉድለት) አለው። ብናምንም ባናምንም÷ ግልጽ ቢሆንም ባይሆንም÷በዛም አነሰም፡ ጉድለት (ሸባነት) አይታጣብንም።

በሕይወታችን ውስጥ መኖሩን ለተረዳነው ችግር መፍትሔ ስንፈልግ፦ ማድረግ ካለብን ነገሮች አንዱ መንስዔውን መረዳት ነው። ለምን እንዲህ ሆንሁ? አንዳንድ ባሕሪዎቼስ ከየት የመጡ ናቸው? ብሎ መመራመርና መረዳት ለችግሩ መፍትሔ ፍለጋ ይረዳል።

ለምሳሌ፦ ቁጡ ከሆንሁ÷ለምን እንዲህ ሆንሁ? በሰው ለመቀየምና ለጥል መፍጠኔ ለምንድን ነው? ፍቅር ለምን ጎደለኝ? በደጅ እንደ ጻድቅ ሰው የምታይ ሆኜ ሳለሁ÷ ቤቴ ስገባ ግን እንደ ነብር በቁጣ ቤተሰዎቼን የማስፈራው ለምንድን ነው? ከሰዎች ጋር መግባባት የተሳነኝ ለምን ነው? ነገሮች አዘውትረው ከቁጥጥር ውጭ የሚሆኑብኝ ለምንድን ነው? በሥራዬ አዘውትሮ የማይሳካልኝ ለምንድን ነው? መታረም የሚገባቸው ባሕሪዎቼ የትኞቹ ናቸው? ይልቁንም ደግሞ በመንፈሳዊ ሕይወቴ እንደሚገባ የማላድገው ለምንድን ነው?

ለመሆኑ እኔም እንደ ሌሎች ሰዎች ጉድለት ይኖርብኝ ይሆን? ወዘተ የመሳሰሉትን ጥያቄዎች በመጠየቅ ራሳችንን ካልተረዳን ድክመቶቻችንን ድል አድርገን ጌታ ወዳሰበልን የድል ሕይወት መድረስ አዳጋች ይሆናል።

እስቲ ሁኔታህን በማስተዋል ተመልከት። ሽባ ሆነህ በመቅደስ ደጅ ምጽዋት የምትለምንበት ነገርህ ምንድን ነው? ከተወለድህ ጀምሮ አብሮህ የኖረና÷የማይፈወስ የመሰለህ በሽታህ (ጉድለትህ) ምን ይሆን?

ራስን መርምሮ ማወቅ፡ ራስን ለማስተዛዘን ከሆነ ፡ ምንም ጥቅም የለውም። ነገር ግን ራስን መርምረው ካወቁ በኋላ፡ “ድካሞቼና ጉድለቶቼ እነዚህ ናቸው። ወደ እነዚህ ችግሮች የገባሁትም በዚህና በዚያ ምክንያት ነው። ከእነዚህ ችግሮቼ ለመውጣት ማድረግ ያለብኝን ነገር ሁሉ አደርጋለሁ፡” ለማለት ከሆነ፤ ግን ራስን መመርመር እጅግ ጠቃሚ የእግዚአብሔር ልጅነት ባሕሪይ ነው።

ማንኛውም ሰው በትክክል ራሱን በሚመረምርበት ጊዜ፦ አዳኝና ረዳት እንደሚያስፈልገው ይገነዘባል። ጌታና አምላክ የሚሆነው÷እግዚአብሔር እንደሚያስፈልገው ያስተውላል። እንዲሁም ከክርስቲያኖች ጋር ሕብረት ማድረግ ይፈልጋል። የክርስቲያኖችም ሕብረት ቅድስናን ለመማማርና ተደጋግፎ በጸጋው ለማደግ ይረዳል። ይህንንም ወደ መረዳት መድረስ የሰው ልጅ በዕድሜው ዘመን ከሚያገኛቸው መልካም ነገሮች ሁሉ ይመረጣል።

እንዲህ ያለህ ሰው የሆንህበት ምክንያት አለ። ይሁን እንጂ የተፈጠርህበትን ምክንያት ደግሞ ብታስተውልና እግዚአብሔር ለሕይወትህ ያለውን ዓላማ ብትረዳ እጅግ ታላቅ ሆኖ ታገኘዋለህ። አሁን ምንም ዓይነት ሰው ልትሆን ትችላለህ፦ ነገር ግን እግዚአብሔር ሲፈጥርህ ሊያደርስህ ወደ አሰበው ክቡር ደረጃ ገና አልደረስህም። ምክንያቱም ገና ተሠርተህ አላበቃህም። ጌታ ለሕይወትህ ከዚህ የበለጠና የተሻለ አሳብ አለው። ያም ገና በሙላት አልተገለጸም።

እስቲ ዛሬ፦ ጉድለቶችህንና መንሥዔዎቻቸውን ስትመረምር÷ በክርቶስ እየሱስ የተጠራህበትን ጥሪውን አስብ ! በሴይጣንና በሁኔታዎች ክፋት የተነሣ÷ ተስፋ ቆርጠህ የተውኸው፦ ወይም በጉድለቶችህ ተደናግጠህ÷ ከጥቂት ሙከራዎች በኋላ የጣልኸው ጸጋ ካለ እስቲ አስብ ! የምናመልከው እግዚአብሔር ተዓምራት አድራጊ አምላክ ስለሆነና የሞተውን እንኳ ማስነሣት ስለማይከብደው በዕምነትና በተስፋ ተነሣ !!

አንተስ “ሽባነቴ የማይፈወስ ስለሆነ÷በመቅደሱ ደጃፍ ተቀምጬ÷የጤነኞች ተመጽዋችና ተመልካች ሆኜ÷ዕድሜዬን ልጨርስ” ብለሃል? ነገር ግን ያኔ በባሪያው በጴጥሮስ ለሽባው የተናገረው ጌታ መንፈስ ቅዱስ፡ ዛሬም ሕያው ስለ ሆነ *“በናዝሬቱ በእየሱስ ክርስቶስ ስም ተነሣና ተመላለስ”* ይልሃል። በቀኝ እጅህም ይዞ ያስነሣሃል። ሽባ የሆንህባቸውም ድክመቶችህ ወደ ብርታት ይለወጣሉ። በዚያም ጊዜ÷ በመቅደሱ ደጅ ሆነህ በመለመን ፈንታ፦ተነሥተህ ወደ መቅደሱ ውስጥ በመግባት ÷ ጌታን ከሚያመልኩት ጋር ቆመህ ታገለግላለህ፡ እግዚአብሔር ይመስገን። ምክንያቱም፦ አንተ በጌታ በየሱስ ክርስቶስ “… ሊገለጥ ካለው ክብር ተካፋይ…” ስለሆንህ ነው። (1ጴጥሮስ 5÷1)

**ሁኔታህ የቱንም ያክል ክፉ ቢሆንም“በናዝሬቱ በእየሱስ ክርስቶስ ስም ተነሣና ተመላለስ” እግሮችህና ቁርጭምጭምትህም ይጽኑ ፤ እግዚአብሔርንም እያመሰገንህ ወደ መቅደሱ ግባ ፤ አንቺም።**

# ምሥጋና

ወንድም ካፕቴን አዲሱ ፌጠነና ቤተሰብ ከዊስኮንስን USA የደብዳቤአችንን ስርጭት ለመደገፍ የላካችሁልን የገንዘብ ስጦታ ደርሶናል፡፡ የምናገለግለው ጌታችን እየሱስ አብዝቶ ይባርካችሁ፡፡

## የድር ገጻችንን ጐብኙ

www.ethiogodslove.org

ገጹን በበለጠ ጠቃሚ ለማድረግ የሚያስችል ምክርና አስተያየት ቢኖራችሁ ጻፉልን፡፡ ጸጋና መንፈስ ቅዱስ የተሞላ አገልግሎት መስጠት እንድንችል ፀልዩልን፡፡ ጌታ በሚያሳስባችሁ ተባበሩን፡፡ ጌታ አብዝቶ ይባርካችሁ፡፡

# እግዚአብሔርን ማምለክ

እግዚአብሔርን በማያመልኩት ላይ "… የእግዚአብሔር ቁጣ ከሰማይ ይገለጣልና …፤" (ወደ ሮሜ ሰዎች 1፥18)

"ሰዎች በክፋታቸው እውነት እንዳይታወቅ ሲያደርጉ በኃጢአታቸውና በክፋታቸው ምክንያት <u>የእግዚአብሐሬር ቁጣ ከሰማይ ይመጣባቸዋል</u>፡፡ የሚመጣባቸውም ስለ እግዚአብሔር ማወቅ የሚገባቸውን እግዚአብሔር ራሱ ገልጦላቸው ያውቁ ስለ ነበረ ነው፡፡ ዓለም ከተፈጠረ ጀምሮ ለሰዎች የማይታየው የእግዚአብሔር ባሕሪይ፥ይኸውም ዘላለማዊው ኃይሉና አምላክነቱ፥እርሱ በፈጠራቸው ነገሮች ግልጽ ሆኖ ታይቶአል፤ ስለዚህ እንደ እነዚህ ያሉት የአዋቂ አጥፊች የሚያመካኙት የላቸውም፡፡ ምክንያቱም እነርሱ እግዚአብሔርን አውቀውት ሳለ ለእርሱ የሚገባውን ክብርና ምሥጋና አልሰጡትም፤ በአሳባቸውም ከንቱ ሆኑ፤ የማያስተውል ልቦናቸውም ጨለመ፤ "ጥበበኞች ነን" ሲሉ ሞኞች ሆኑ፡፡ ዘላለማዊ የሆነውን እግዚአብሔርን በማምለክ ፈንታ አላፊና ጠፊ በሆኑት፡- በሰው (የመላዕክትና የቅዱሳን ሥዕል)፥በወፍ፥በእንስሳ፥በመሬት ላይ በሚሳቡ ፍጥረቶች መልክ የተሠሩትን ምሥሎች ማምለክ ጀመሩ፡፡ ስለዚህ እርስ በርሳቸው አሳፋሪ ድርጊቶችን እንዲፈጽሙ፥ እግዚአብሔር ርኵሰት ለሞላበት ለክፉ ምኞታቸው ተገዥዎች እንዲሆኑ ተዋቸው፡ ይህም የሆነው የእግዚአብሔርን እውነት በሐሰት ስለ ለወጡ፥በፈጣሪ ፈንታ ፍጡርን ስላመለኩና ስለ አገለገሉ ነው፤እግዚአብሔር ግን ለዘላለም የተመሰገነ ነው፤ አሜን፡፡"

"ሰዎች እግዚአብሔርን ለማወቅ ስላልፈለጉ አስነዋሪ ነገር እንዲያደርጉ እግዚአብሔር ለማይረባ አእምሮ አሳልፎ ሰጣቸው፡፡ ስለዚህ በግፍ፥ በክፋት፥ በስስት፥በቂም፥ በምቀኝነት፥ በነፍሰ ገዳይነት፥ በጥል፥ በአታላይነት፥ በክፉ ጠባይ ሁሉ የተሞሉ ናቸው፤እንዲሁም ሐሜተኞች፥ የሰውን ስም የሚያጠፉ፥ እግዚአብሔርን የሚጠሉ፥ ሰውን የሚያዋርዱ፥ ትዕቢተኞች፥ትምክሕተኞች፡ ክፋትን ለማድረግ ዘዴ የሚፈልጉ፥ ለወላጆቻቸው የማይታዘዙ፥የማያስተውሉ፥ውል የሚያፈርሱ፥ ፍቅር የሌላቸው፥ጨካኞች ናቸው፡፡ 'እነዚህን ነገሮች የሚያደርጉ ሁሉ ሞት ይገባቸዋል' የሚለውን የእግዚአብሔርን ሕግ እያወቁ ይህን ሁሉ ያደርጋሉ፤ ማድረግ ብቻ ሳይሆን እንዲህ የሚያደርጉትንም ሰዎች ያበረታታሉ፡፡"

(ወደ ሮሜ ሰዎች 1፥18-31 አዲሱ ትርጉም)

"ተግሣጼን ለመቀበል ፈቃደኛ አይደለህም፤ትዕዛዜንም ትንቃለህ፡፡ ሌባውን ስታይ ከእርሱ ጋር ትወዳጃለህ፤ ከአመንዝሮችም ጋር በመስማማት ትተባበራለህ፡፡ክፉ ቃል ለመናገር ዘወትር ዝግጁ ነህ፤ ሐሰትንም ከመናገር አትቈጠብም፡፡የገዛ ወንድምህን ለመክሰስና ለማሳጣት ዘወትር የተዘጋጀህ ነህ፡፡ ይህን ስታደርግ ዝም በማለቴ እኔም እንደ አንተ የሆንሁ መሰለህን? አሁን ግን ፊት ለፊት ነገሩን ገልጬ እገስጽሃለሁ፡፡ ስለዚህ እናንተ እኔን የምትንቁ ሁሉ ይህን ስሙ፤ አለባለዚያ አጠፋችኋለሁ፤የሚያድናችሁም የለም፡፡"

(መዝሙረ ዳዊት 50፥17-22)

ከዚህ በላይ ከመጽሐፍ ቅዱስ የተጠቀሱትን ስናነብብ የራሳችን ሕዝብ ይታሰበናል፡፡ ምክንያቱም የእኛን ሰው በሦስት ከፍሎ በዚህ በእግዚአብሔር ቃል መመዘን ስለሚቻል ነው፡፡

አንዱ ክፍል፡- "በትውልዴም ክርስቲያን ነኝ፥ በእየሱስ አምናለሁ" የሚል፥ ሆኖም ግን በኑሮው እግዚአብሔር ከሚጠላቸው ነገሮች አንዱንም የማይጸየፍ፥ እንዳሻው ኗዋሪ ነው፡፡ በዚህ ሰውና በኮሚኒስት ወይም በዚህ ሰውና ጣዖት በሚያመልኩት መሐከል ምንም ልዩነት የለም፡፡ ስለዚህ ይህ ሰው ለእግዚአብሔር ቁጣ ራሱን አዘጋጅቷል፡፡

ሌላኛው ክፍል ደግሞ፡- በምንም በማንም የማይመስለውንና እርሱ ብቻ መመለክ የሚገባውን "እግዚአብሔርን በማምለክ ፈንታ አላፊና ጠፊ በሆኑት በሰው፥በወፍ በእንስሳ፥በመሬት ላይ በሚሳቡ ፍጥረቶች መልክ የተሠሩትን ምሥሎች" የሚያመልኩት ናቸው፡፡በእነዚህም ላይ "የእግዚአብሔር ቁጣ ከሰማይ ይገለጣል" ምክንያቱም "በላይ በሰማይ ካለው፥ በታችም በምድር ካለው፥ ከምድርም በታች በውኃ ካለው ነገር የማንኛውንም ምሳሌ (የቅዱሳንም የመላዕክትም) የተቀረጸውንም ምስል ለአንተ አታድርግ"ተብሎ ተጽፎአል፡፡

(ኦሪት ዘዳግም 5፥8)

ሦስተኛው ክፍል ግን የኮሚኒስታዊ ፍልስፍና ውላጅ፥ በምሑራዊነት የክሕደት መንፈስ ተደግፎ የሚሠራ፥ ዕውቀት መሰል ድንቁርና ነው፡፡ ፊደል ያልቆጠሩትም ዘበናውያን ሳይቀሩ ጌታ እየሱስን ተቀብለው እግዚአብሔርን ላለማምለክ የሚሰጡት ምክንያት ነው፡፡ ለምሳሌ፡- የማኅበረሰብ ፍትሕ መጓደል እግዚአብሔር ባለመኖሩ ነው ይላሉ፡፡ አንዳዴም "እግዚአብሔር ለመኖሩ ምንም ማስረጃ የለንም" ይላሉ፡፡ በዙሪያቸው የከበባቸውን የእጁን ሥራ ፍጥረቱን ሁሉ ሆን ብለው አያስተውሉም፡፡ በእነዚህም "የእግዚአብሔር ቁጣ ከሰማይ ይገለጣል"፡፡ ምክንያቱም፡- "አሁን ያሉ ሰማያትና ምድር ግን እግዚአብሔርን የማያመልኩት ሰዎች እስከሚጠፉበት እስከ ፍርድ ቀን ድረስ ተጠብቀው በዚያ ቃል <u>ለእሳት ቀርተዋል</u>"

(2 ጴጥሮስ 3፥7)

<u>"ለአንዳንዶች የሚዘገይ እንደሚመስላቸው ጌታ ስለ ተስፋ ቃሉ አይዘገይም፥ ነገር ግን ሁሉ ወደ ንስሐ እንዲደርሱ እንጂ ማንም እንዳይጠፋ ወዶ ስለ እናንተ</u> ይታገሣል፡፡" (2ጴጥሮስ 3፥9)

# እግዚአብሔርን ማምለክ እንዴት ነው?

ለሰው ደኅንነት ከእግዚአብሔር የተሰጠውን <u>የእየሱስ ክርስቶስን አዳኝነት</u> <u>አምኖ መቀበልና በትምሕርቱ መኖር</u>፡፡

በመጽሐፍ ቅዱስ መሠረት <u>እግዚአብሔር ከማይወደው አኗኗር ተቆጥቦ መኖር</u>፡፡

<u>ስለ ጌታ እየሱስ ክርስቶስ አዳኝነት ላላመኑት ሁሉ በመመስከር</u> ዕለት ዕለት እየተጉ መኖር፡፡

ከአማኞች ጋር በመተባበር (ቤተክርስቲያን) በመጽሐፍ ቅዱስ ጥናት፥ በፆምና ጸሎት፥ በመዝሙር፥ አሥራት በመክፈል፥ ድሖኖችን በመርዳትና ከሰው ሁሉ ጋር በሰላም በመኖር ወዘተ ነው፡፡ አንተ እንዲህ ታመልካለህ? አንቺስ?

## የዳነ ሰው መዳኑን ያውቃል፡፡

ንስሐ ገብተህ በእየሱስ ክርስቶስ በኩል የተሰጠውን ምሕረት ሳትቀበል፥ ቤተ ክርስቲያን በመመላለስና በማሽብሽብ ጊዜህን ታባክናለህ? ደኅንነት ሳይቀበሉ ሰውን እንጂ እግዚአብሔርን ማታለል አይቻልም፡፡ ለምንስ ይጠቅማል፡፡ ምሕረትን የተቀበለ ሰው ግን በግልጽ መዳኑን ያውቃል፡ ያልዳነ ሰውም በነፍሱ ውስጥ ምስክርነት ስለሌለው አለመዳኑን ያውቃል፡፡ አንተስ? <u>ድነሃል</u>? የዳኑት ሰዎች ተመልካችና አጃቢ ሆነህ ከማለፍ ለራስህ መዳን ትችላለህ፡ በጌታ በእየሱስ ክርስቶስ ዕመን ትድናለህ፡፡

"በእርሱ የሚያምን ሁሉ የዘላለም ሕይወት እንዲኖረው እንጂ እንዳይጠፋ እግዚአብሔር አንዲያ ልጁን እስኪሰጥ ድረስ ዓለሙን እንዲሁ ወዶአልና፡፡"

(የዮሐንስ ወንጌል 3፥16)

## ስለ ኃጢአትህ እየሱስ ሞቶልሃል፡፡

"ገና ደካሞች ሳለን ክርስቶስ ዘመኑ ሲደርስ ስለ ኃጢአተኞች ሞቶአልና፡፡"

(ወደ ሮሜ ሰዎች 5፥6)

## <u>ዕምነትና ምስክርነት ለደኅንነት</u>

"እየሱስ ጌታ እንደ ሆነ በአፍህ ብትመሰክር እግዚአብሔርም ከሙታን እንዳነሣው በልብህ ብታምን ትድናለህና፤ <u>ሰው በልቡ አምኖ ይጸድቃልና በአፉም መስክሮ ይድናልና</u>፡፡"

(ወደ ሮሜ ሰዎች 10፥ 9-10)

"መዳንም (ከየሱስ በቀር) በሌላ በማንም የለም፡ እንድንበት ዘንድ የሚገባን ለሰዎች የተሰጠ ስም ከሰማይ በታች ሌላ የለምና፡፡" (የሐዋሪያት ሥራ 4፥12)

## የንስሐ ፀሎት

ጌታ እግዚአብሐር ሆይ፥ እስካሁን ድረስ አንተን ሳላመልክ በመኖሬ ይቅር በለኝ፡፡ ጌታ እየሱስ ሆይ፥አሁን የልቤን ደጅ እከፍትልሃለሁ፡፡ ሕይወቴንም ለመንግሥትህ እንድታዘጋጅ እፈቅድልሃለሁ፡፡ ከዛሬ ጀምሮ አንተን በማምለክ ራሴን ከሚመጣው ቁጣ ማዳን ስለምሻ ተቀበለኝ፡፡ ስለ ስምህ፡ አሜን፡፡

# እየሱስ ጌታ ነው፡፡ ጌታ ይባርክህ፡፡